# በቤጂንግ ኢፌዲሪ ኤምባሲ በሊቢያና ደቡብ አፍሪካ በአሰቃቂ ሁኔታ ለተገደሉ ኢትዮጵያውያን ሻማ የማብራትና የህሊና ፀሎት ሥነ-ሥርዓት ተካሄደ፣

ሚያዝያ 16 ቀን 2007 ዓ.ም ቤጂንግ በሚገኘው ኢፌዲሪ ኤምባሲ አዘጋጅነት በደቡብ አፍሪካ በተቀሰቀሰው ዘረኝነት፣ እንዲሁም በሊቢያ ላይ ራሱን ISIS ብሎ በሚጠራው ፅንፈኛ አሸባሪ ቡድን በዜጎቻችን ላይ የፈፀመውን አሰቃቂና ኢ-ሰብአዊ ግድያ በማውገዝ የህሊና ፀሎት፣ ሻማ የማብራትና የክብር መዝገብ የመፈረም ሥነ-ሥርዓት ተካሂዷል፡፡



በፕሮግራሙ ላይ የኤምባሲው ዲፕሎማቶች፣ ቤጂንግና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልድ ኢትዮጵያውያን፣ በቻይና በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ተገኝቷል፡፡ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት ምክትል የሚሲዮን መሪ አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ በደቡብ አፍሪካ በዘረኝነት መነሻ በዜጎቻችን ላይ በተፈፀመው ኢ-ሰብአዊና ጭካነ የተሞላበት ግድያ፣ እንዲሁም በሊቢያ ላይ አይኤስ የተባለ ፅንፈኛ አሸባሪ ቡድን በኢትዮጵያውያን ላይ በፈፀመው አሰቃቂ ግድያ የተሰማቸውን ጥልቅ ሀዘን ገልፀው ድርጊቱን በጽኑ አውግዘዋል፡፡ በመቀጠልም በሊቢያና በደቡብ አፍሪካ በግፍ የተገደሉ ወገኖቻችን በጋራ እናስባቸዋለን፣ እንደ አገርና እንደ ህዝብ የተደቀነብን አደጋ ስለሆነ በጋራ እንመከተዋለን ብለዋል፡፡

አያይዘውም የኢትዮጵያ መንግሥት በስደት የሚገኙ ዜጎቻችንን በፍላጎታቸው ላይ ተመርስቶ ወደ አገራቸው ለመመለስ ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ ሽብርተኝነትን ከመታገል አንፃር የነበረውን ጽኑ አቋም አውስተው የፀረ-ሽብር ትግሉ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልፀዋል፡፡

በዚህም ተሳታፊዎቹ በክብር መዝገቡ ላይ ካሰፈሯቸው አስተያየቶች መካከል፣ ጥቃቱ የተሰነዘረው ለመላው ኢትዮጵያ ህዝብ በመሆኑ በጋራ እንመከተዋለን፣ ይህ የኢሰብአዊ ድርጊት የአገራችንን የሐይማኖታዊ መቻቻልና በልዩነት ላይ የተመሠረተ አንድነት ላይ የሚያመጣው ምንም አይነት ተፅዕኖ አይኖርም፣ ይልቁንም መቻቻላችንንና አንድነታችንን ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የበለጠ የሚያጠናክር ይሆናል የሚሉ ይገኙበታል፡፡ በተሳታፊዎቹ በዚህ ዘግናኝ ግድያ ህይወታቸው ላለፉ ሰማዕታት የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት ተደርጎ ሻማ የማብራት ሥነ-ሥርዓት ተካሂዷል፡፡




በመጨረሻም ተሳታፊዎቹ በተዘጋጀው የሀዘን መግለጫ ክብር መዝገብ ላይ ጥልቅ ሀዘናቸውን በመግለፅ፣ ለሟች ቤተሰቦች፣ ለዘመድ አዝማድና ለወዳጆች፣ እንዲሁም ለመላው ኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትን ተመኝቷል፡፡

ኢፌዲሪ ኤምባሲ ቤጂንግ